# *የባልና ሚስት ስብእና በትዳር ግንኙነት ላይ ያለው ተጽዕኖ*

*ከበደ በከሬ (kbtuli@ethionet.et: 251-911-316756)*

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስህተት የሚፈጽሙት በሌሎች ሰዎች ግፊት ሲደረግባቸውና በስሜት ውስጥ እንዲገቡ ሲደረጉ ነው፡፡ በተለይ ያ ግፊት የሚያደርግባቸው ሰው የሚወዱት ወይም የሚያከብሩት ሰው ሲሆን ግፊቱ ኃይለኛ ይሆንና ያንን ሰው የሚያስደስት እርምጃ ይወሰዳል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውሳኔ የሚሰጠው በግል በማሰብና ስላመኑበት ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ምሪት ነው፡፡

ባልና ሚስት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ እኩል ሰብዓዊነት ያላቸው ወንድና ሴት ናቸው፡፡ በትዳር ግንኙነት ውስጥ አንዱ የሌላው ረዳት በመሆን ኑሮን አብረው ይገፋሉ፡፡ የአንዱ ድካም በሌላ ጥንካሬ እየተሸፈነ፣ አንዱ ሌላውን እንደ ባልንጀራ እየቀረጸ የሕይወት ሕልማቸውን ከግብ ለማድረስ አብረው ይጓዛሉ፡፡ በዚህ ግንኙነትና አብሮ ተጓዥነት ወቅት ብዙ ውጣ-ውረዶች ያጋጥማቸዋል፡፡ ሆኖም በፍቅር ሆነው በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት የገቡትን ቃልኪዳን በማሰብና በአንድነት ከመኖርም የተሻለ አማራጭ አለመኖሩን በመረዳት አብረው ይዘልቃሉ፡፡

ባልና ሚስት በትዳር ውስጥ ከሚኖራቸው ሚና በተጨማሪ በተሰማሩባቸው የግል መስኮችም ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በትዳር ጉዳይ ባልና ሚስት ተስማምተው መወሰንና መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ትዳራቸውም ስኬታማ ይሆናል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው፡፡ ባል በሚሠራበት መሥሪያ ቤት ሚስት ወይም ሚስት በምትሠራበት መሥሪያ ቤት ባል ጣልቃ በመግባት በሥራዎቻቸው ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የባልና ሚስት ግንኙነትን ከመጉዳቱም ባሻገር ሥራውንና ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰዎች፣ ቡድኖችንና ኅብረተሰቡን አልፎም ሀገርን የሚጎዳ ነገር ሊፈጠር ይችላል፡፡

ከማግባቴ በፊት በአብዛኛው በዐውዳችን የወንድ የበላይነት እንዳለ ስለሚነገር ባል ሚስቱን እንደሚያሸንፍ አስብ ነበር፡፡ በትዳር ሕይወት ውስጥ ብዙ በቆየሁ መጠን ግን ይህ ሐሳብ ትክክለኛ አለመሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ ባል የሚስቱን ቃል ባይሰማና በራሱ መንገድ ቤተሰብን መምራት ቢፈልግ እንዲሁ ይለፋል እንጂ አይሳካለትም፡፡ የመጀመሪያው ነገር በዚህ መንገድ ሚስቱን በማሸነፍ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የእርስዋን ፍቅርና ወዳጅነት በማግኘት ሰላማዊ ሕይወት ሊኖረው አይችልም፡፡ በኃይል ከእርስዋ የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ማግኘት ቢችል እንኳ እርካታ ግን አይሰጠውም፡፡ ሰው የሚረካው ከሌላው የሚፈልገውን ነገር በኃይል ሳይሆን በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ፍቅር ሲያገኝ ነው፡፡ ስለዚህ ባል ደስተኛ የሚሆነው ለሚስቱ ሲገዛ ወይም ሲሸነፍ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ለሚስቴ ስሸነፍ ሳተርፍ፣ ሚስቴን ሳሸንፍ ደግሞ ሲከሰር አይቻለሁ፡፡ ባለቤቴ በጉልበት፣ በትምህርት ደረጃ፣ በደመወዝ፣ በዕድሜ፣ (ሌላም መጨመር ይቻላል) አትበልጠኝ፤ ነገር ግን ታሸንፈኛለች፡፡



ለእርስዋ ተሸንፌ መኖር የሕይወት መርህዬ እንዲሆን አድርገአለሁ፡፡ ሰው ገብቶት በኃይል ሳይሆን በፍቅር ለሌላው በመሸነፍ ሰላማዊ ሕይወት መኖር ሲችልና ሌላው ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖር ሲፈቅድ ቤተሰብ የእረፍት ቤት ይሆናል፡፡

በባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ አንዱ ለሌላው መሸነፍ አስፈላጊ ቢሆንም አንዱ የሌላውን ሐሳብ ለመቀበልና ለማስተናገድ ሁለቱም የሚስማሙበት እሴት መኖር አለበት፡፡ አንዳቸው ወይም ሁለቱም አንድን ሐሳብ በስምምነት መቀበላቸው ብቻ ሳይሆን ያ ሐሳብ ከተቀበሉት እሴት አንጻር ያለውን ተገቢነት መመርመር ይኖርባቸዋል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የሕይወታቸው መመሪያ ያደረጉ ባልና ሚስት የእያንዳንዳቸውን ሐሳብ ከዚያ አንጻር በማየት እንደ ቃሉ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሁለቱ ሐሳብ ዳኛ የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት ባል ሚስቱ ክፉ ነገር እንድታደርግ ወይም ሚስት ባሏ ክፉ ነገር እንዲያደርግ ቢመክሩ የተመከረው ወገን የትዳር ጓደኛን ለማስደሰት ብሎ ተግባራዊ ማድረግ የለበትም፡፡ የባልን ወይም የሚስትን ሐሳብ/ምክር/ዕቅድ መጽሐፍ ቅዱስ የማይደግፍ ከሆነ የትዳር ጓደኛ ያንን ሐሳብ በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ መቀበል የለበትም፡፡ እንዲህ ዓይነት ልዩነት ሲፈጠር ግን ሁኔታውን በጥበብ መያዝ መቻል አስፈላጊ ነው፡፡ አንዱ ወገን መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም ሌላውን ገንቢ ባልሆነ መንገድ መቃወም ቢጀምር ግንኙነትን ያበላሻል፤ አልፎም ትዳርን ወደ ማፍረስ ደረጃ ሊያድግ ይችላል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በባልና ሚስት መካከል ባለው ግንኙነት ሚስቱ የምትነዳውና እርሱም በሚስቱ የሚነዳ ባልና ሚስትን ታሪክ እናገኛለን (1ነገ16-21)፡፡ የባል ስም አክዓብ ሲሆን የሚስቱ ስም ደግሞ ኤልዛቤል ትባላለች፡፡ አክዓብ ከይሁዳ ተገንጥሎ የራሱን መንግሥት የመሠረተው የሰሜኑ ክፍል ንጉሥ ነበር፡፡ ለሃያ ሁለት ዓመት በሰማርያ ንጉሡ ሆኖ የገዛ ሲሆን ዘመኑ ከእግዚአብሔር ጋር የተመቻቸ አልነበረም፡፡ አክዓብ አንድ ዋና ችግሩ የነበረው ከእርሱ ቀደም ብሎ የነበረው እጅግ ክፉ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ያደረገውን የኢዮርብዓምን ኃጢአት እንደ ቀላል ነገር መቁጠሩ ነበር (1ነገ16:31)፡፡ ሚስትም ያገባው ከሲዶናውያን ወገን ነበር፡፡ በግሉ በዓልን ማምለክ ጀመረ፤ ይህም ብቻ ሳይሆን የጣዖት አምልኮ በግዛቱም ውስጥ እንዲስፋፋ ምክንያት ሆነ፡፡ በዚህ ድርጊቱ ደግሞ ከእርሱ ቀደም ብሎ ከነበሩት ነገሥታት ሁሉ ይልቅ «እግዚአብሔርን ለቁጣ የሚያነሳሳ ድርጊትን ፈጸመ» (1ነገ16:33)፡፡

አክዓብ በእግዚአብሔር ፊት ከፈጸማቸው ክፉ ሥራዎች መካከል ብዙዎቹ በሚስቱ በኤልዛቤል አነሳሽነት፣ ግፊት ወይም መሪነት የተፈጸሙ ነበሩ፡፡ ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹን መመልከት እንችላለን፡፡

(1) *የእግዚአብሔርን ነቢያት ማስገደል* (18:13)፡ ይህ ድርጊት የተፈጸመው በግልጽ ነበር፡፡ ምክንያቱም በቤተ መንግሥት ውስጥ የሚያገለግለው አብድዩ ይህን ያውቅ ነበር፡፡ እርሱ በዚያን ወቅት

መቶ የሚሆኑትን ነቢያትን ከሞት ለማዳን የተለያዩ ጥረቶችን ያድርግ እንደ ነበር ለነቢዩ ኤልያስ ነግሮታል።

(2) *የራስዋን ነቢያት በቤተ መንግሥት መቀለብ* (18:19)፡ በኤልዛቤል ትዕዛዝ በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆነው የሚቀለቡ ወደ ስምንት መቶ የሚሆኑ የጣዖት አምልኮ አገልጋዮች/ነቢያት ነበሩ። እነዚህ በምድረ እስራኤል የበኣልን አምልኮ የሚያስፋፉ ሚስዮናውያን ነበሩ።

በዚያን ዘመን የእግዚአብሔር ነቢይ የነበረው ኤልያስ ሰዎች በሁለት ሐሳብ ከሚዋልሉ ከበኣልና ከእግዚአብሔር አምላክ የሆነውን እንዲያመልኩ ለአክዓብ ሐሳብ አቀረበ። አክዓብም  በጉዳዩ ተስማምቶ የበኣል አገልጋዮችና ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተወራረዱ። ሁለቱም ወገን መስዋዕት አዘጋጁና በእሳት የሚመልስና መስዋዕቱን በእሳት የሚባለው እርሱ አምላክ ነው አሉ። በመጨረሻ የኤልያስ አምላክ በእሳት መለሰ፤ ሕዝቡም እርሱ አምላክ ነው በማለት ለእግዚአብሔር ሰገደለት። ኤልያስ በዚያኑ ዕለት ብዙ የኤልዛቤል ጣዖት አገልጋዮችን አስገደለ (18:40)።

አክዓብ ወደ ቤቱ ሲመለስ «ኤልያስ ያደረገውን በሙሉ፣ ነቢያቱንም ሁሉ እንዴት በሰይፍ እንዳስገደላቸው ለኤልዛቤል *ነገራት»* (19:1)። አክዓብ እንደ ባል ውሎውን ለሚስቱ አጭር ሪፖርት የሚያቀርብ ሰው ነበር። ኤልዛቤ ግን አንድ ጥሩ ያልሆነ ባሕርይ ነበራት። ባልዋ በሥራ ቦታ ያጋጠመውን ነገር ለእርስዋ ሲያጫውታት ከእርሱ ጋር ተወያይታ እንዴት ሁኔታዎችን በጥበብ መያዝ እንደሚገባው ከመምከርና ስሜቱንም ከመደገፍ ይልቅ በራስዋ እርምጃ ለመውሰድ ትነሳለች። አንደኛው ስለ ኤልያስ በሰማችው ታሪክ እርሱን ለማስገደል መነሳትዋ ነበር (19:2)። ኤልያስ የኤልዛቤል የዛቻ መልዕክት እንደ ደረሰው ሸሸ። ኤልዛቤል አንድን ነገር ለማድረግ ወደ ኋላ እንደማትመለስ ወይም አክዓብም ሐሳብዋን ሊያስቀይራት እንደማይችል ገብቶታል።    እርሱን ግን ልታገኘው አልቻለችም።

ሁለተኛው እጅግ የሚያሳዝነው የናቡቴ የወይን ቦታ ጉዳይ ነው። ናቡቴ የሚባል ሰው ከቤተ መንግሥት አጠገብ የወይን ቦታ ነበረው። ንጉሡ አክዓብ ቦታውን በለውጥ ወይም በገንዘብ ለመግዛት ናቡቴን ጠየቀው። ናቡቴ ግን ርስቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልነበረም። ንጉሥ የአንድን ገበሬ የወይን ሥፍራ ጠይቆ እምብ ተባለ። አክዓብ ከናቡቴ አዎንታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ ተባሰጨ፣ ተቆጣ፣ ወደ ቤቱ ገብቶ ምግብ ሳይበላ ተኛ። ይህ ሲሆን ሚስቱ ኤልዛቤል ወደ ንጉሥ ክፍል ገብታ «እስከዚህ የተበሳጨኸው፣ ምግብስ የማትበላው ለምንድነው?» በማለት ጠየቀችው። አክዓብም የናቡቴን የወይን ቦታ ጠይቆ አዎንታዊ መልስ እንዳላገኘ ነገራት።

ሚስትም ይህን ከሰማች በኋላ «አንተ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ትባላለህ?» አለችው። ምን ማለትዋ ነው? ንጉሥ ሥልጣን ስላለው በፈለገው መንገድ የፈለገውን በእጁ ማስገባት ይችላል። ለንጉሥ የማይቻል



ነገር የለም። ንጉሥ ጠይቆ አንድ ገበሬ እንዴት እምቢ ይለዋል? አክዓብ የንጉሥነት ሥልጣኑን በመጠቀም የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ የተሣነው ሰው እንደሆነ ለመግለጽ ይህን ሐሳብ ነገረችው። ባል የንጉሥነት ሥልጣኑን እንደሚፈልገው መጠቀም ሲያቅተው ሚስት ደግሞ በሥልጣኑ በመጠቀም እርሱን ደስ ለማሰኘት ቆርጣ ተነሳች። ሐሳቡንም «በል ተነሣና እህል ቅመስ፣ ደስም ይበልህ፣ የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ እኔ እንድታገኝ አደርግሃለሁ» (21:7) በማለት ነገረችው። ሕዝቡ ሳሙኤል ንጉሥ እንዲሾምላቸው በጠየቁት ወቅት ሳሙኤል ንጉሥ የወደደውን የወይንና የእርሻ ቦታዎቻቸውን እንደሚወስድባቸው ነገሮአቸው ነበር (1ሳሙ8:14)። የንጉሥ ሥልጣን አይከለከልም። አሁን ንጉሡ ሥልጣኑን ለራሱ ጥቅም በሥራ ላይ ማዋል ሲያቅተው ሚስት ነቀፈችው።

ኤልዛቤል ሚስቱ እንደ መሆኗ መጠን ባሏ በሥራ ሂደት በገጠመው ሁኔታ ተበሳጭቶና ተናድዶ በሚመጣበት ጊዜ የስሜት ድጋፍ በመስጠት ማጽናናቷ መልካም ነገር ነው። ከቁጣው የተነሣ ምግብ ለመብላትም ፈቃደኛ ስላልነበረ እህል እንዲቀምስ አደፋፈረችው። እርሱን ያጽናናችው ደግሞ እርሱ ያልቻለውን ነገር በማድረግ የሚፈልገውን በእጁ ለማስገባት እንደምትችል ተስፋ በመስጠት ነበር። «አንተ የፈለገውን ማግኘት አልቻልክም፤ እኔ ግን በእጅህ አስገባለሁ» በሚል ሐሳብ ባሏን አጽናናችው። ሚስቱ ኤልዛቤል በእርሱ ፈንታ ሆና ለማድረግ ያሰበችውን ነገር ብትነግረውም አክዓብ ግን ምንም አልተናገራትም። ሚስቱ የናቡቴን የወይን ተክል ሥፍራ እንዴት አድርጋ በእጁ ልታስገባ እንደምትችል አልጠየቃትም። እርሷም ብትሆን ግቡን እንጂ ሂደቱን አልነገረችውም።

አክዓብ የናቡቴን የወይን ቦታ ለማግኘት የሄደበት ሂደት መልካም ነበር። ወደ ናቡቴ በመሄድ የወይን ቦታውን እንዲለውጠው ወይም በገንዘብ እንዲሸጥለት ጠየቀው። ንጉሡ ለምን እንደሚፈልገውም ሁለት ምክንያቶችን አቀረበለት። አንደኛው የወይን ቦታው በቤተ መንግሥት አጠገብ ነው። ሁለተኛ ደግሞ ንጉሡ ያንን ሥፍራ የእርሻ ቦታ ሳይሆን የአትክልት ሥፍራ የማድረግ ዕቅድ ነበረው። ለናቡቴም ሁለት አማራጮችን ሰጠው፡ የተሻለ የወይን ሥፍራ ለመስጠት ወይም በገንዘብ ከእርሱ መግዛትን አቀረበለት። መቼም ከንጉሥ አንጻር ሲታይ ንጉሡ እነዚህን አማራጮች በማቅረቡ መልካም ነገር አድርጓል። በሥልጣኑ ናቡቴን አፈናቅሎ የወይን ቦታውን በኃይል መውሰድ ይችላል። ምስኪኑ ናቡቴ ምንም ሊያደርገው አይችልም ነበር። የንጉሡ አካሄድ በጎ ቢሆንም የናቡቴ መልስ ግን አሉታዊ ነበር። ናቡቴ ቦታውን እንደ ቅርስ ወይም ርስት በማየቱ ለመለወጥም ለመሸጥም አልፈለገም። «ዐፅመ ርስቴን» በማለት ነበር ቦታውን የገለፀው። ቦታው ለናቡቴ ከእርሻ ቦታነት ያለፈ ትርጉም ነበረው።

አክዓብ ሚስቱ ኤልዛቤል ላቀረበችው ሐሳብ ምንም ጥያቄ አላቀረበም። «እኔ እኮ በዚህና በዚያ መንገድ በመሄድ ለማግባባት ቢሞክረው እምቢ አለኝ፤ አንቺ እንዴት አድርገሽ ትወስጃለሽ?» ብሎ ቢጠይቃት ኖሮ ያሰበችውን እርምጃዎች ትነግረውና ይነጋገሩበት ነበር። ይህ ደግሞ የንጉሥነት ሥልጣኑንም ለግል ጥቅሙ ብሎ ሕዝቡን እንዳይበድል

ለማድረግ፣ ነገሮችን እንደ እግዚአብሔር ሕግ ለመመዘንና እርስዋም ባሏን ለማስደሰት ብላ ክፉ ድርጊት እንዳትሠራ ለመከላከል ያግዝ ነበር። አክዓብ ኃላፊነት ነበረበት። ሚስቱ የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓትን አታውቅም። ስለዚህ እርሱ የቤተሰቡንና የመንግሥቱን አካሄድ ከሕግና ሥርዓቱ አንጻር በመመልከት መምራት ነበረበት። ዜግነቷ የሌላ ሀገር ስለሆነች ለሕዝቡ እንደ እርሱ ላትራራ እንደምትችል መገመት ነበረበት። እነዚህን ሐሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት «እንዴት?» የሚል ጥያቄ ቢጠይቃት ኖሮ ሊመጣ ያለው ስህተት እንዳይፈጸም መከላከል ይችል ነበር።

ባል የጀመረውን ጉዳይ እርሱ ራሱ ቢጨርሰው የተሻለ ነበር። «እንደ ጀመርኩት እስቲ ደግሞ ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም እሞክራለሁ» በማለት ሐሳብ ቢሰጣት ኖሮ እርስዋ በእርሱ ፈንታ ሆና እርምጃ ለመውሰድ አትነሳም ነበር። ናቡቴ በመልካም መንገድ ሥፍራውን እንዲለቅ ማድረግ የሚቻልበትን ስልት ካላት ደግሞ ለባልዋም መንገር ትችል ነበር። እርሱም ቢሆን «ምን የተሻለ መንገድ መጠቀም ይገባኛል? ምን ትመክሪኛለሽ?» ብሎ አልጠየቃትም። ባሏ በራሱ ያልቻለውን ነገር እንዴት ማግኘት እንደሚችል የጥበብ መንገድን ማሳየት ብትችል ኖሮ ጥበበኛ ሴት ትባል ነበር። አሁን ግን ለመውሰድ ያቀደችው እርምጃ ክፉ እንጂ ጥበበኛ የሚያደርጋት አካሄድ አይደለም። ባልም ቢሆን ሚስቱን ወደ መልካም ነገር የሚመልስ ሳይሆን ባሰበችው መንገድ እንድትሄድ የሚለቅ ሰው ነበር። «ይህ በጎ ነገር አይደለም» የሚል አቋም አልነበረውም።

ኤልዛቤልም «በአክዓብ ስም ደብዳቤዎችን ጻፈች፣ በገዛ ማኅተሙም አትማ» ለሽማግሌዎችና ለመኳንንት ላከች። በዚህ ደብዳቤ ውስጥም ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ተብሎ የሐሰት ምስክሮች መስክረውበት በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል የሚያዝ መልዕክት ተጽፏል። የታዘዙት ሰዎች በትዕዛዙ መሠረት በመሄድ ናቡቴን አስገደሉ። ምክንያቱም ደብዳቤዎቹ ኦፊሴላዊ ነው። የንጉሡ የአክዓብ ማኅተም አርፎበታል። የምትሠራውን ተንኮል በራሷ ሳይሆን አክዓብንም በማስገባት ትሠራ ነበር። ከዚያም የናቡቴን መሞት የምሥራች ለኤልዛቤል መልዕክተኛ ልኮውባት ነገሩአት። የናቡቴ መገደል የመጨረሻው ግብ አልነበረም። ኤልዛቤል ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ መሞቱን ለአክዓብ ነገረችው። አክዓብ አሁንም «እንዴት?» ብሎ አልጠየቀም። ከዚያም በኋላ ሚስቱ ኤልዛቤል አክዓብን ናቡቴ በገንዘብ አልሸጥልህ ያለውን በነጻ መውረስ እንደሚችል ነገረችው። ሄዶም እንዲወርሰው ባዘዘችው መሠረት ተነስቶ ወደ ናቡቴ እርሻ ሄደ። በእነርሱ ቀመር ነገር ሁሉ ተመቻችቶ ውርስ ላይ ደርሷል። ምናልባት አክዓብ ወደዚያ ሥፍራ ሲሄድ እንዴት አድርጎ ቦታውን ጥሩ የአትክልት/መዝናኛ ሥፍራ እንደሚያደርግ ሳያስብ ይቀራል? ንጹሕን ደም በሐሰት በማፍሰስ የናቡቴን የወይን ቦታ ለውረስ እዚያ ሲደርስ ያልጠበቀው ነገር ገጠመው።

አክዓብ መቋቋም ያልቻለው፣ ኤልዛቤልም ለማስገደል ያልቻለችው እርሱ እንደ ጠላት የሚቆጥረው ኤልያስ በእግዚአብሔር ተልኮ በዚያ ሥፍራ ብቅ አለ። አክዓብ ኤልያስን ሲያየው ነገሩ ገባው። ኤልያስንም «ጠላቴ ሆይ



አገኘኸኝን» አለው። እውነት ለመናገር ለአክዓብ ጠላቱ ሚስቱ ኤልዛቤል እንጂ ኤልያስ አልነበረም። ኤልያስ እርሱ ሲስት መንገዱን እንዲያስተካክል የእግዚአብሔርን አቅጣጫ የሚያሳየው ነቢይ ነበር። አሁን ግን አክዓብ ለኤልያስ በዒላማ ውስጥ ገብቶለት ጠብቆታል። አክዓብም ኤልያስ ለምን እንደ መጣ በግልጽ ያውቃል። አካሄዱና ሥራው ክፉ ነበር። ንጹሕ ደም በማፍሰስ ርስት ለመውረስ በመምጣቱ አክዓብና ሚስቱ በሁለት ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ነው። የመጀመሪያው በግድያ ወንጀል ሲሆን ሁለተኛው የሰውን መሬት በሕገ-ወጥ መንገድ ለመውሰድ በመምጣቱ ነበር። ለዚህ ሁሉ ያደረሰችው ደግሞ ሚስቱ ነበረች። በእርግጥ አክዓብ ሚስቱ እንዲህ ያለውን ክፉ ድርጊት እንዳትሠራ የራሱን ኃላፊነት መወጣት ይችል ነበር። እርሱ ንጉሥ እንዲሁም ባል በመሆኑ ለናቡቴ መሞት ተጠያቂ እንደሆነ እግዚአብሔር በኤልያስ በኩል በግልጽ ነገረው።

አክዓብ በሚስቱ በመነዳቱ እንዲሁም ሚስቱም በፈለገችው መንገድ በመሄዷ ለቤተሰቡ፣ ለኅብረተሰቡም የሚጠቅም መልካም ነገር አልተደረገም። የሕይወት ዘይቤያቸው ለጊዜው በሰላም አብረው እንዲኖሩ ያደረገ ቢመስልም በዘላቂነት ግን እነርሱንና ሌሎችንም የሚጠቅም ሆኖ አልተገኘም። የሁለቱም መጨረሻቸው አሳዛኝ ነበር። አክዓብ በሰማርያ በጦርነት ላይ እያለ ተገደለ። ከዚያም ውሾች ደሙን ላሱት። በግፍ ለመውሰድ ባሰበው ናቡቴን በገደለበት ሥፍራ ለመሞት እንኳ ዕድል አላገኘም።

ኤልዛቤል አክዓብ ከሞተ ለአሥራ አራት ዓመት ያህል ኖረች። ሰብዓዊ ፍጡር መሞቱ የማይቀር ቢሆንም የኤልዛቤል አሟሟት እጅግ አሳዛኝ ነበር። በሞቷ ቀን ኢዩ ወደ እርስዋ እንደሚመጣ ስትሰማ ዐይኗን ተኳኩላ፣ ጠጉሯንም አሰማምራ በመስኮት ትመለከት ነበር። የንጉሥ ልጅና የንጉሥ ሚስት መሆኗን ለማሳየት ሆን ብላ ያደረገችው ድርጊት ነበር። ላደረገችው ክፉ ሥራዎች ምንም ዓይነት ፀፀት ሳይሰማት ግትር አቋሟን ይዛ እስከ መጨረሻው ቆየች። ኢዩን ስታይ «ጌታህን የገደልህ አንተ ዘምሪ የመጣኸው በሰላም ነውን?» ብላ ጠየቀችው። ይህ የሽሙጥ አነጋገር ነበር። ኢዩን ዘምሪ ብላ ጠራችው። ዘምሪ ከእርሱ ቀደም ብሎ የነበረውን ንጉሥ በመግደል ሥልጣን የያዘና ለአንድ ሳምንት ብቻ መንገሥ የቻለ ሰው ነበር። በኢዩ ትዕዛዝ የገዛ አገልጋዮቿ በመስኮት በኩል ወደ ምድር ወረወሩአት። ከዚያም ደሟ በግድግዳውና በመሬት ላይ ተረጨ። ኢዩ እዚያው ጥሏት ሄደ። በኋላ ግን «ምንም ቢሆን የንጉሥ ልጅ ናትና ይህችን የተረገመች ሴት በሚገባ ቅበሯት» በማለቱ ለመቅበር አስከሬንዋን ለማንሳት ሲሄዱ ከሦስት ብልቶቿ ውጭ ምንም አላገኙም። ደሟን ውሾች ላሱት። ተገቢውንም የቀብር ሥርዓት ሳታገኝ ቀረች (2ነገ.9፡ 30-37)።፡

አክዓብ ለምን በሚስቱ ተነዳ? እርሷስ ለምን ነዳችው? ባልና ሚስት አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው የማይቀር ጉዳይ ነው። ሆኖም ሚዛን በመጣስ አንዱ በሌላው እንዲነዳ ሲያደርግ ግን ጤናማነት አይደለም። በአክዓብና ኤልዛቤል ሁኔታ ዋነኛ ምክንያት የሆነው የስብእና አለመጣጣም ነው። የሁለቱንም ሰዎች ታሪክ ስንመለከት ሁለቱ የተለያየ ስብእና

እንዳላቸው መረዳት እንችላለን:: አክዓብ የተገዥነት ስብእና ሲኖረው ኤልዛቤል ደግሞ የመቆጣጠርና የመግዛት ዓይነት ስብእና አላት:: ባል እሺ የሚልና ሌላውን ላለማስከፋት/ ለማስደሰት የሚኖር ዓይነት ሰው ነው:: ከሦስት ዓመት ድርቅ በኋላ ኤልያስን ሲያገኝ «እስራኤልን የምታውክ አንተ ነህን?» (18:17) በማለት ጠየቀው እንጂ ክፉ ነገር አላናገረውም:: ከዚያም ኤልያስ ነቢያትን በቀርሜሎስ ተራራ እንዲሰበስብ ሲነግረው እሺ ከማለት ውጭ ምንም አላለም:: ሕዝቡንና ነቢያትን ጠራለት:: የበኣል ነቢያትንም ሲያሳርድ ምንም አልተናገረም:: ሚስቱም በኤልያስ ላይ ዝታ መልክተኞችን ስትልክበት አልተቃወመም::

የሚገርመው የሶርያ ንጉሥ ብርና ወርቅ፣ ሚስቶቹና ልጆቹን የእርሱ እንደሆኑ መልዕክተኞችን ሲልክበት «ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ ልክ እንዳልኸው ነው እኔም ሆንሁ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው» (20:4) በማለት መለሰለት:: ወሰኑን በማበጀት ንጉሡን «ይህን አትችልም» ማለት አልቻለም:: ጉዳዩ እየጠነከረ ሲመጣ ለሽማግሌዎቹ ሲያቀርብ እነርሱ ሐሳቡን እንዳይቀበል መከሩት:: «እሺ አትበለው» ያሉት እነርሱ ናቸው እንጂ እርሱ ይህን ለማለት አቅም አልነበረውም:: በናቡቴ የወይን ቦታ ጉዳይም አክዓብ በድርድርና ሰላማዊ መንገድ ቦታውን ለመውሰድ ፈልጎ ነበር:: ግን አልተሳካለትም:: በዚህም ቢሆን በራሱ ተቆጥቶ ወደ ቤቱ ገባ እንጂ ጥፋት አላደረገም:: ሚስቱ እርምጃ ለመውሰድ ስትዘጋጅም «ይህ ነገር መልካም አይደለም» አላላትም:: ስለዚህ አክዓብ የሚነዳው ሰው ሲያገኝ የሚነዳ እንጂ ራሱ ሰዎችን ወደሚፈልግበት የሚነዳ ዓይነት ስብእና አልነበረውም::

ከዚህም በተጨማሪ አክዓብ የአኩራፊ ልጅ ዓይነት ባሕርይ ነበረው:: አኩራፊ ልጅ አንዳንድ ነገሮች እርሱ በሚፈልገው መንገድ ካልሄደለት ያኮርፋል:: ለራሱ የሚመቸውን ዓለም በመፍጠር መኖር ይፈልጋል:: ወላጆቹ ምግብ እንዲበላ ቢጠይቁት እሺ ብሎ አይበላም:: አክዓብ በዕድሜው ጎልማሳ፣ ባለትዳርና በሥራው ደግሞ ሀገርን የሚያስተዳድር ሰው ቢሆንም ባሕርይው እንደ ሕጻን ነበር:: በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በራሱ ላይ የደረሰውን ነገር ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁ ያደርጋል:: ይህ ብስለት የሌለውና በራሱ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ሰው መሆኑን ይገልጻል::

ሚስቱ ኤልዛቤል ደግሞ አክራሪ ሃይማኖተኛ ነች:: የባሏን አምላክ ከማምለክ ይልቅ የራሷን ሃይማኖት ይዛ ለመቆየት የወሰነች ሴት ነች:: ሃይማኖቷን ይዞ መኖር ብቻ ሳይሆን በምድረ እስራኤል ለማስፋፋትም ቆርጣ ተነሳች:: ይህንንም ተልዕኮ የሚያስፈጽሙትን ወደ ስምንት መቶ የሚሆኑ ነቢያትን ከሀገሯ አስመጣች:: እነርሱን በቤተ መንግሥት በማስቀመጥ ትመግባቸው ነበር:: ለእነዚህ ተቀናቃኝ ሊሆኑ የሚችሉ የእስራኤል አምላክ ነቢያትን አስቀድማ አስገድላለች:: ስለዚህ የበኣል ነቢያት እነዚህን የተገደሉትን ነቢያትን የተኩ ነበሩ::

ኤልዛቤል ኃይለኛ፣ የእርሷን ሐሳብ እምቢ የሚለውን በኃይል ለማንበርከክ እርምጃ የምትወስድና የምትደርስበትን ግብ እንጂ በሂደት



ለሚሆኑ ነገሮች ደንታ የሌላት ጨካኝ ሴት ነች:: ይህን ኃይለኛነት ከአባቷ ሳትማር እንዳልቀረች መገመት ይቻላል:: አባቷ አምባገነን ሲሆን በሲዶና የንጉሥነት ሥልጣንን በኃይል የጨበጠ ሰው ነበር:: በዚህ አምባገነን አባት ሥር ማደግ ምን ዓይነት ባሕርይ ሊያስተምር እንደሚችል ማስተዋል ይቻላል:: ባሏ እንደ እርሷ በኃይል ሳይሆን በድርድር ሄዶ የሚፈልገውን ማግኘት ባለመቻሉ «አንተ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ትባላለህ?» ትለዋለች(21:8):: እርሱም የእርሷን ዘይቤ እንዲከተል ለማድረግ በእርሱ ላይ ጫና ታሳድራለች:: የምትፈልገውን ነገር በራሷ ማድረግ እንደምትችል ትተማመናለች:: መቼም አንድ ባል በሚስቱ እንዲህ ተብሎ ሲነቀፍ በውስጡ «በእርግጥ እኔ ወንድ አይደለሁም ማለት ነውን?» የሚል ጥያቄ ሳይፈጠርበት አይቀርም:: በሚስቱ ፊትም ወንድነቱን/ባልነቱን/ ንጉሥ መሆኑን ለማስመስከር ቀደሞ ከሄደበትና ካልተሳካለት አካሄድ በተቃራኒው እርምጃ እንደሚወስድ አያጠራጥርም:: በዚህ ሂደት የእርሱ አካሄድ የሚመራው ሚስቱ ያለችውን ሐሳብ ከግብ ለማድረስና በእርሷ ፊት ሞገስ ለማግኘት እንጂ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር መመልከት አይታይም:: አክዓብን ግን የኤልዛቤል ወቀሳ አላንቀሳቀሰውም:: ከዚህም የተነሣ በራሷ እርምጃ ለመውሰድ ተነሳች::

ኤልያስንም «ነገ በዚህ ሰዓት ያንተንም ነፍስ ከእነዚህ እንደ አንዱ ሳላደርግ ብቀር...» (19:2) በማለት ምላ ዛተችበት:: ኤልያስም የእርሷን ስብእና ስለሚያውቅ ፈርቶ ሸሸ:: በናቡቴ የወይን ቦታ ጉዳይም ለባሏ «እኔ እንድታገኝ አደርግሃለሁ» (21:8) በማለት በድፍረት ተናገረች:: «እኔ አደርጋለሁ»፣ «እኔ እችላለሁ» የሚል አቋምና አስተሳሰብ አላት:: በእርግጥ ከዚህ ስብእናዋ አንጻር ስንመለከተው በቤተሰብ ወይም በሀገር ደረጃ ሥልጣን በማን እጅ እንዳለ በግልጽ ማወቅ ይቻላል:: ዕቅዷን ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውንም መንገድ ትጠቀማለች:: ናቡቴን ለማስገደል ዕቅድ ስታወጣ ጾም እንዲታወጅ አድርጋ ነበር:: ከእርሱ ኃጢአት የተነሣ በእስራኤል ላይ ትልቅ አደጋ ሊመጣ እንደሚችል ለማስመሰል የተጠቀመችበት መንፈሳዊ ስልት ነበር:: ስለ እግዚአብሔር ነገር ግድ የሌላት የራሷ አማልክት ያላት ብትሆንም አሁን ባለችበት ዐውድ የልቧን ለማድረስ ሕዝቡ በመለመደውና በሚቀበለው ስልት ገባችበት:: በዚህም ስኬታማ ሆናለች::

ኤልዛቤል እልህኛ ስለሆነች ነው እንጂ የናቡቴ የወይን ቦታ ነፍስ የሚያስገድል ነገር አይደለም:: ለአትክልት ቦታ የምትሆን ትንሽ መሬት ለማግኘት ተብሎ ሰውን መግደል የኤልዛቤል እና የባሏንም የሞራል አቋም ምን ያህል የወደቀ እንደሆነ ያሳያል:: በእርግጥ ይህን ስንመለከት አክዓብ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር ለማድረግ ራሱን የሸጠ ሰው መሆኑን እንረዳለን:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱ ሴቶች እንደ ኤልዛቤል አንገተ-ደንዳና፣ በምንም ዓይነት መንገድ የራሷን ፈቃድ እውን ለማድረግ ጽኑ አቋም ያላት ሌላ ሴት አልተጠቀሰችም::

ባልና ሚስት በስብእና ተመሳሳይ እንዲሆኑ ማድረግ አይቻልም:: በስብእና መጣጣማቸውን መፈተሽ በቅድመ ጋብቻ ወቅት ሊያስቡበት የሚገባ ነገር ነው:: ከተጋቡ በኋላ ግን ልዩነቱን ማጥፋት ባይችሉም ልዩነቱ

በትዳራቸው፣ አልፎም በማሕበራዊና በሥራቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያስከትል ገንቢ በሆነ መንገድ መያዝን መማር ይችላሉ:: ብዙውን ነገር ከተግባራዊ ሕይወታቸው የሚማሩ ቢሆንም የማማከር አገልግሎት ማግኘትም ስለ ስብእናውና አያያዙ የበለጠ ለማወቅ ያግዛቸዋል::

አክዓብና ኤልዛቤል በስብእና ይለያያሉ:: አክዓብ በውስጣዊ ማንነቱ ደካማ ሰው ሲሆን ኤልዛቤል ደግሞ ጠንካራ ሴት ነበረች:: ሁለቱን አንድ የሚያደርጋቸው ግን ክፉዎች መሆናቸው ነው:: ሁለቱም ክፉ ነገርን ለማድረግ ራሳቸውን የሰጡ ናቸው:: ከሁለታቸው «ይህ እኮ መልካም አይደለም» ሲል የሚቃወም ሰው አልነበረም:: የትዳር ጓደኛ ሌላውን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማወቅ በግንኙነት ውስጥ የሚከሰቱትን አንዳንድ ሁኔታዎችን በመመልከት ማወቅ ይቻላል:: እነዚህ ሁኔታዎች አንድ ጊዜ የተፈጸሙ ከሆኑ ስብእናውን አይገልጹትም፤ ነገር ግን ዘወትር የሚደረጉ ዓይነት ሲሆኑ የዚያ ሰው ባሕርይ መሆናቸውን እንረዳለን::

*በትዳር ጓደኛ ግፊት ስህተት ውስጥ ላለመግባት ምን መደረግ አለበት?*

የትዳር ጓደኛሞች በጣም የሚቀራረቡ ጥንድ ከመሆናቸው የተነሣ አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ማድረጉ የማይቀር ጉዳይ ነው:: ይህም መሠረታዊ ሐሳብ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በአሉታዊ ግፊት ስህተት ውስጥ ላለመግባት መከተል የሚገባቸው መርሆዎች መኖር አለባቸው:: ሁለቱም በእነዚህ መሠረታዊ መርሆዎች ላይ በመስማማት እርስ በርሳቸውን ከስህተት መጠበቅ ይችላሉ:: ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሐሳቦች ማስተዋል ሁለቱም ወሰናቸውን ጠብቆ እንዲሄዱ ያግዛቸዋል::

*አዎንታዊ ተጽዕኖ አስፈላጊ ነው፡-* በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ሰዎች መካከል ጓደኞቻችንና የሥራ ባልደረቦቻችን የሚጠቀሱ ናቸው:: ከሁሉም በላይ ግን እንደ ትዳር ጓደኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር አይኖርም:: ባልና ሚስት ብዙ ጊዜ አብረው ማሳለፍ ባይችሉ እንኳ አብረው የሚያሳልፉት ጊዜ ጥራት ያለው ይሆናል:: በሁለቱ መካከል ጥልቀት ያለው ግንኙነት በሚኖርበት ጊዜ አንዱ ሌላው ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ዕድሉ ከፍ ይላል:: እኛ በትዳር ጓደኞችን ወይም የትዳር ጓደኞችን በእኛ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳደር መቻላቸው መልካም ነገር ነው:: በአስተሳሰብ፣ በባሕርይና በግንኙነት ላይ መልካም ነገር ማድረግ እንድንችል የሚያግዙን ሰዎች እንፈልጋለን:: በዚህ መልኩ የሚቀርጹን የትዳር ጓደኛ ማግኘት መታደል ነው:: እንዲህ ያለውን አዎንታዊ ተጽዕኖ መቀበል፣ ማክበርና መፍቀድም አስፈላጊ ነው:: እነዚህ ነገሮች ለእኛ ጥቅም በመሆናቸው ልንወዳቸው ይገባናል:: እስቲ ከትዳር ጓደኞችን ጋር በመኖራችን በአስተሳሰባችን፣ በባሕርያችንና በግንኙነታችን ላይ የመጣውን አዎንታዊ ተጽዕኖ እንቁጠር:: በማስተዋል ብንመለከት ብዙ ነገሮችን ማውጣት እንችላለን::

ባሎች ሚስቶቻቸው በሕይወታቸው ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማድረግ እንዲችሉ ሲፈቅዱላቸው የትዳር ሕይወታቸው ፍሬያማ ይሆናል:: በዚህ ዓይነት ግንኙነት ውስጥ የሚገኙ ሚስቶች ባሎቻቸውን ይወዱአቸዋል፣



ያከብሩአቸዋል:: በትዳር ውስጥ ግጭትን ሊፈጥር የሚችል ጉዳይ ሲነሳም ባሎቻቸውን በክፉ ከመናገርና መጥፎ እርምጃ ከመውሰድ ይቆጠባሉ:: ቀድሞ የነበረው ግንኙነታቸው አስቸጋሪ የሆኑትን ጉዳዮች በተረጋጋ መንፈስ ውስጥ ሆነው እንዲፈቱ ይረዳቸዋል:: ሚስቶች ባሎቻቸው ሆን ብለው እነርሱን ወደሚፈልጉበት አቅጣጫ ለመጠምዘዝ እንደማይከራከሩአቸው ይገነዘባሉ:: ከዚህም የተነሣ ለሚስቶቻቸው መልካም ሐሳብ እሺ የሚሉ ባሎች በጥሩ የትዳር ሕይወት ውስጥ ይኖራሉ፤ ሚስቶቻቸውም ደስተኞች ይሆናሉ::

ለሚስት ሐሳብ እሺ ማለት ወይም በሚስት አዎንታዊ ተጽዕኖ ሥር ለመዋል መፍቀድ ማለት ሁሉን ነገር እሺ ማለት አይደለም:: የራስን ስብእና/አስተሳሰብ ትቶ በሚስት መነዳት ማለት አይደለም:: ባል ሙሉ በሙሉ ሚስቱ እንድትመራው እጁን አጣጥፎ መቀመጥ አይደለም:: ለሚስትም እንዲሁ ነው:: ሁለቱም የየግል ኃላፊነት አላቸው:: አንዱ በሌላው ላይ መልካም ተጽዕኖ በማሳደር ግንኙነታቸውን በዘላቂነት መጠበቅ፣ ወዳለሙት የሕይወት ግብ አብረው መጓዝና አንዱ ሌላውን በመደገፍ በጥምረት ይኑሩ ማለት ነው:: ይህን ለማድረግ ባልና ሚስት አብረው ጊዜ ማሳለፍ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እርስ በርስ መነጋገር፣ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ አንዱ የሌላውን ሐሳብ መፈለግና ማግኘት፣ በትሕትና መቀራረብና ፍርሃትን ማስወገድ ይገባቸዋል:: በጥልቀት መተዋወቅና መቀራረጽ የሚመጣው በእነዚህ ነገሮች በማደግም ጭምር ነው::

*አሉታዊ ተጽዕኖን መቋቋም ይገባል፡-* በትዳር ግንኙነት ውስጥ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሕይወትን ያሳድጋል፣ ወደ ተሻለ ብስለት ይለውጣል:: በተቃራኒው ስንመለከት አሉታዊ ተጽዕኖ ሕይወትን ይጎዳል:: በትዳር ውስጥ አንዱ ወገን በሌላው ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና የሚያሳድር ከሆነ ያ ግንኙነት ጤናማ አይደለም:: የትዳር ጓደኛ ሌላውን ከመጠን በላይ በመቆጣጠር፣ አንድን ነገር ሳይፈልግና ሳይፈቅድ የግድ በዚያ ግንኙነት ውስጥ ለመኖር ብሎ የሚያደርግ ሲሆን መላ መፈለግ አለበት:: ተገቢ ያልሆነ ጫናን ከሚያሳድር የትዳር ጓደኛ ጋር መኖር ሁልጊዜ በታፈነ ቤት ውስጥ እንደ መኖር ያህል ነው:: ንጹሕ አየር በሌለበት ቤት ውስጥ መኖር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ንጹሕ አየርን ተንፍሶ የሚያውቅ ሰው ያውቀዋል:: በግንኙነቱ ውስጥ ወሰን የሚባል ነገር አይታሰብም:: አንዱ ወገን የሌላውን የግል ነጻነትን ይዳፈራል:: ራስን ለዚያኛው ወገን በማስገዛት እንጂ ራስን ሆኖ መኖር አይታሰብም:: እንዲህ ዐይነት ባሕርይ ያለው ሰው የትዳር ጓደኛን ማንኛውንም የሕይወት እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ይሻል፣ ጥረትም ያደርጋል::

ከቁጥጥር ብዛት የተነሣ በትዳር ጓደኞቻቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ባሎች ወይም ሚስቶች ቅንዓት ያለባቸው ናቸው:: ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ማንም ሰው እንዲቀርብ አይፈልጉም:: ከዚህም የተነሣ «ዛሬ ማን ነው የመጣው?» «ከማን ጋር ነበር ስታወራ/ስታወሪ የነበረው?» «ለምን ቆየህ/ሽ?» በማለት ይጠይቃሉ:: በዛሬው ዘመን ደግሞ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ያለው ሰው የባልን ወይም የሚስትን ተንቀሳቃሽ ስልክ በማውጣት

ማን እንደ ደወለና ለማን እንደ ተደወለ መረጃ ለማግኘት ይፈልጋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው በትዳር ጓደኛው ሕይወት ውስጥ ራሱን ብቻ ማየት ይሻል፡፡ የትዳር ጓደኛው ዓለም ውስጥ ገዝፎ ሲታይ ደስታን ያገኛል፡፡ እነዚህን ባሕርያት በሚያሳይበት ወቅት በሌላ መልኩ ደግሞ በራስ መተማመን የሌለው፣ ተጠራጣሪና ስለ ራሱ ዋስትና የማይሰማው ምስኪን ሰው መሆኑን መግለጡ ነው፡፡

የትዳር ጓደኞቻቸውን ከመጠን በላይ የሚቆጣጠሩ ሰዎች ባሎቻቸውን ወይም ሚስቶቻቸውን ይወዳሉ፡፡ እንዲህ ማድረጋቸውም አንዳንድ ጊዜ አለማክበራቸውን አያመለክትም፡፡ ሆኖም ቁጥጥሩ የሚያፈቅርና የሚያከብር ሰው ያደርጋል ተብሎ የሚታሰብ ባለመሆኑ ለግንኙነት መዳበር ያስቸግራል፡፡

*በእምነት/ሃማይኖት ላይ መስማማት፡-* ባልና ሚስት በምርጫቸው የተለያየ ሃይማኖት በመያዝ ተጋብተው ወይም ከተጋቡ በኋላ የተለያየ ምርጫ በማድረግ በሃይማኖት ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ለትዳር ሕይወታቸው እርካታና ዘላቂነት ሁለቱም አንድ ሃይማኖት ቢከተሉ የሚመረጥ ቢሆንም ይህ በማይቻልበት ሁኔታ ቤተሰባቸውን በምን ዓይነት እሴት ማስተዳደር እንደሚገባቸው መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲህ ካልሆነ በአንዱ ሃይማኖት ትክክል የሆነው ነገር፣ በሌላኛው ሃይማኖት ደግሞ ትክክል እንዳልሆነ ሊቀጠር ስለሚችል የጋራ ውሳኔ ማድረግ አዳጋች ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የገዥነት ስብእና ያለው የትዳር ጓደኛ የራሱን በሌላው ላይ በመጫን ሌላውን በራሱ መስመር ይነዳል፡፡

*የትዳር ጓደኛን ምርጫ መስፈርት ማስተካከል፡-* ይህ ላለገቡ ሰዎች የሚሆን ምክር ነው፡፡ አክዓብ የሚስት ምርጫ ያደረገው ከሲዶናውያን የፖለቲካ ትስስር ለማድረግ ነበር፡፡ የኤልዛቤልን ባሕርይ/ስብእና አላጠናም፡፡ ለትዳር ደስታና ዘላቂነት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው የሁለቱ ተጋቢዎች የስብእና መጣጣም በመሆኑ የትዳር ጓደኛ ምርጫ ሲደረግ በውጫዊ ነገሮች ላይ ትኩረት ከማድረግ በውስጣዊ ባሕርያት ላይ መመርኮዝ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለማግባት የሚታስቡት ሰው ስብእና ከእናንተ ጋር የማይጣጣም ከሆነ ያለማችሁትን የትዳር ሕይወት እንዳትኖሩ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በውጭ ከሚታዩት ነገሮች ይልቅ ውስጣዊ ማንነታቸውን ማጥናት ትዳራችሁ የሕይወት ግባችሁን እንድታገኙ የሚያግዝ ኅብረት ይሆናል፡፡

### *ባለትዳር የሆኑ ባል ወይም ሚስት በሚሠሩበት ሥራ ላይ የትዳር ጓደኞቻቸውን ምን ያህል ማሳተፍ ይገባቸዋል?*

የባሎች ወይም የሚስቶች በሥራ ቦታ ያለውን መረጃ ከማካፈል ጀምሮ እስከ ውሳኔ ሰጪነት ደረጃ ምን ያህል ቢያሳትፉ ጠቃሚ ይሆናል? ከተጨባጭ ዐውዳዊ ነባራዊ ሁኔታ ስንነሳ አብዛኛዎቹ ባለትዳሮች ስለ ሥራቸው ዝርዝር ነገር ለትዳር ጓደኞቻቸው አያካፍሉም፡፡ ሆኖም አልፎ አልፎ አንዱ በሌላው ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል



መገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ባል በሚስት ወይም ሚስት በባል ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ መከተል የሚገባቸው ጠቃሚ ምክሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

*የባልና ሚስት መቀራረብ ይወስናል፡-* ባልና ሚስት በዐውዳቸው ጥሩ የሚባል ግንኙነት ሲኖራቸው በአብዛኛው አንዱ ለሌላው ስለ ሥራው ሁኔታ ያካፍላል፡፡ በሥራ ቦታ የተከሰተውን ነገር ሁሉ በዝርዝር ሳይሆን በዕለቱ ስላገጠሙና ትኩረት ስለተሰጠባቸው ነገሮች መረጃን ይለዋወጣሉ፡፡ ባልና ሚስት ከሥራ መልስ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የጋራ ጊዜ ሲኖራቸው ስለ ቀን ውሎአቸው አብረው ይጫወታሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ላይ ምግብ የሚያበስሉ ሲሆን ምግቡን እያበሰሉ አንዱ «ዛሬ እንዴት ነበር?» ሲል ጨዋታው ይጀመራል፡፡ እራት ሲበሉም እርስ በርስ መነጋገር ይችላሉ፡፡ ከዚያም ጊዜ እስከሚፈቅድላቸው ያህል ያወራሉ፡፡

ሚስት የቤት እመቤት ከሆነች ደግሞ ባል በመሥሪያ ቤቱ የሆነውን ነገር ሊያካፍላት ይችላል፡፡ ባልና ሚስት ስለ መሥሪያ ቤታቸው ሁኔታ ምን ያህል እንደሚነጋገሩ ለማወቅ ያነጋገሩአቸው አንዳንድ ሰዎች ስለ ሥራቸው እርስ በርስ የሚነጋገሩት በጣም ጥሩ ወይም መጥፎ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከወትሮ የተለየ ትኩረትን የሚስብ ነገር ሲያጋጥም ስለ ጉዳዩ ያወራሉ፡፡ በአብዛኛውም ከሥራ መልስ በሚያገኙት ጊዜ ስለ ኑሮአቸው፣ ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና ግላዊ ጉዳዮችን አብረው ያወራሉ፡፡ ስለ ሥራም በሚነሳበት ጊዜ ስለ ሥራው ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ የሚያወሩት በሥራ ቦታ ስላሉ ሰዎች ሕይወትና ከእነርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

*የመረጃውን ተገቢነት/ጠቃሚነት መፈተሽ፡-* አንድ ባለትዳር በሥራ ቦታ ያለውን መረጃ በሙሉ ለትዳር ጓደኛው አያካፍልም፡፡ በዕለት ተዕለት ከሚያጋጥሙ ነገሮች መካከል ለእርሱ/ለእርሷ ተገቢ ነው የሚባለውን ብቻ ያካፍላል፡፡ በሥራ ቦታ ያሉ ነገሮች ሁሉ ለትዳር ጓደኛ መነገራቸው ተገቢ ወይም ጠቃሚ የማይሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ከሥራ ሂደት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ያለውን ግላዊ ሁኔታ ለእርሱ ወይም ለእርሷ ማካፈል ይጠቅም ይሆናል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ከሥራ ጋር የተያያዙትን መረጃ ለባለቤቱ ለማካፈል ሲፈልግ መጠየቅ ከሚገባቸው ጥያቄዎች አንዱ «ይህ መረጃ ለትዳር ጓደኛ ቢነገረው/ቢነገራት ምን ይጠቅማል?» የሚለውን ነው፡፡ እውቀትን ከማስጨበጥ፣ ጥንቃቄን/ትጋትን/ ለመጨመር፣ ባሕርይን ከመለወጥ፣ ጥበብን ከመስጠት፣... አንጻር ጠቀሜታ እንዳለው ከታሰበ መረጃውን ማካፈል አስፈላጊ ነው፡፡ ስለ ሥራ ዝርዝር ነገሮችን ሁልጊዜ ማካፈል በትዳር ጓደኛ ላይ የማያስፈልግ ጫና መጣል ነው፡፡ የትዳር ጓደኛን የሥራ ቦታ/ቢሮ ችግሮች ማራገፊያ ሥፍራ ከማድረግ ለመቆጠብ ተገቢውንና ጠቃሚውን መረጃ አስቀድሞ መለየት መቻል ያስፈልጋል፡፡

*የትዳር ጓደኛችንን ብስለት ማጤን፡-* በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ አንዳንድ ነገሮች ውስብስብና በቀላሉ የሆነ ስሜት ውስጥ ሊያስገቡን የሚችሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ከአለቃችን ጋር በሥራ ላይ አብዛኛውን ጊዜ የምንጋጭ

ቢሆን እንዲህ ዓይነት መረጃን ለትዳር ጓደኛችን ለማካፈል ስናስብ «ይህን መረጃ እንዴት ያስተናግድ/ታስተናግድ ይሆናል?» ብለን መጠየቅ ይገባናል:: ካሳለፍነው ግንኙነት በመነሳት የትዳር ጓደኛችንን የብስለት ደረጃ ስለምናውቅ በዚያው መሠረት ጠቃሚና ተገቢ የሆነውን መረጃ ማካፈል ይቻላል::

*ሁሉም ነገር ለትዳር ጓደኛ መነገር የለበትም:-* እንዲህ ዓይነት መርህ ያላቸው ባልና ሚስት የራሳቸው ወሰን ይኖራቸዋል:: አንዱ ለሌላው ተገቢ ነው ብሎ የሚያስበውን ሐሳብ ያካፍላል፤ ሌላውም እንዲሁ ያደርጋል:: በዚህ ግንኙነት ባል ወይም ሚስት የራሳቸውን መረጃ ለራሳቸው መያዛቸው እንደ ትልቅ ችግር አይታይም:: በአብዛኛው እንዲህ ዓይነት ዘይቤ የሚከተሉ ሰዎች ከሚሠሩት ሥራ ወይም ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር በተገናኘ ምስጢርን ለትዳር ጓደኛቸው ማካፈል በሥራቸው ወይም በአገልግሎታቸው ላይ ሊያስከትል ከሚችለው ጉዳት በመነሳት ሊሆን ይችላል:: የሙያው ወይም የአገልግሎት ሥነምግባሩ የደንበኞችን/ ተገልጋዮችን ምስጢር መጠበቅን የሚጠይቅ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው እንጂ ለትዳር ጓደኛም ስለ ሰዎች መረጃ መስጠት ከሥነምግባሩ አንጻር ተገቢ አይደለም:: ሰዎች እነዚያን ባለሙያዎች ወይም አገልጋዮች አምነው የነገሩአቸውን ምስጢር ለሦስተኛ አካል አሳልፎ መስጠት በደል ነው:: ይህን ማድረግ ለህሊናም ሲባል አለማድረጉ ጠቃሚና በታማኝነት ለመኖር ይረዳል:: እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባል ወይም ሚስት አንዱ በሌላው ሥራ ላይ ጣልቃ ለመግባት ዕድል አይኖረውም:: አጠቃላይ ስለ ሥራው እንጂ ስለ ዝርዝር ሁኔታዎች መረጃ ስለማይሰጣቸው በቀጥታ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉበት ሁኔታ አይኖርም::

*የትዳር ጓደኛ ብቃት:-* ባል ወይም ሚስት ለሚሠሩት ሥራ አንዳቸው ለሌላኛው ድጋፍ የማድረግ ብቃት ሲኖራቸው በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙትን ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ማካፈል ይጠቅማል:: በእንዲህ ዓይነት መልክ ሲታይ አንደኛው የትዳር ጓደኛ ለሌላው እንደ አማካሪ ሊሆን ይችላል:: የባልና ሚስት ሙያ ተመሳሳይ ሲሆን ወይም ሁለቱም በተመሳሳይ የሥራ መደብ ለምሳሌ በመሪነት ላይ ያሉ ሲሆን መረጃን እርስ በርስ መለዋወጥ አስፈላጊ ነው:: ይህ ሲደረግ አንደኛው ወገን ምክር ለማግኘት ብሎ በሥራ ቦታ ያጋጠመውን ነገር ለትዳር ጓደኛው ያካፍላል:: በዚህም መሠረት ሌላውም ከሙያው ወይም ከልምድ ያገኘውን እውቀት/ግንዛቤ ለሌላው በማካፈል እንዲጠቀምበት ይረዳል:: አንዱ በሌላው ላይ ጫና አያደርግም:: ከመጀመሪያው መረጃው የወጣው በአንዱ ወገን ፈቃደኝነትና «ልጠቅመኝ የሚችል ምክር ሳገኝ እችላለሁ» ከሚል ዓላማ የተነሣ በመሆኑ አሉታዊ ጫና አይኖርበትም::

*ስለሥራ ለትዳር ጓደኛ አለማካፈል ጉዳት አለው:-* ብዙ ጊዜአችንን የምናሳልፈው ሥራ ቦታ ነው:: በሳምንት አምስት ቀን፣ በቀን ደግሞ ስምንት ሰዓት በሥራ ቦታ እንገኛለን:: በዚያ ሥፍራ የሚያጋጥሙን ነገሮች በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ያመጣሉ:: በሥራ ቦታ የሚያጋጥሙትንና በዚያ ሥፍራ ማውራት የማንችላቸውን ጉዳዮች ይዘን ወደ ቤት መጥተን ለትዳር



ጓደኛችን ማካፈል መቻል መፍትሔ ባይሰጥም አንዳንድ ጊዜ እፎይታን ይሰጣል:: እንዲህ ማድረግ የሚቻለው ጥሩ አድማጭና ሁኔታውን በመከታተል ራሳችንን ማየት እንድንችል የሚያግዘን የትዳር ጓደኛ ስኖረን ነው:: በአብዛኛው ባሎች በሥራ ቦታ ያጋጠማቸውን ችግር ለሚስቶቻቸው አይናገሩም:: ጉዳዩን በራሳቸው መፍታት ስለሚፈልጉና ከሚስትም ምክር መቀበልን እንደ በታችነት ስለሚቆጥሩ ቢያንስ ተናግረው እፎታ ማግኘት ሲችሉ ከነ ችግሩ ለብዙ ጊዜያት ይመላለሳሉ:: ያልተፈታ ችግር ይዞ መመላለስ ደግሞ ጤንነትንና የትዳር ግንኙነታቸውን ይጎዳል::

እንግዲህ በባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ማድረግ የማይቀር ጉዳይ ነው:: ይህ ተጽዕኖ አዎንታዊ እንዲሆን እያንዳንዱ ማድረግ የሚገባው ጥንቃቄና ጥበቃ ቢኖርም ግንኙነቱ የሚመራበት እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ መመሪያ መኖሩ ጠቃሚ ነው:: በዚህ ግንኙነት ውስጥ ስብእና የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ስለሚሆን አንዱ የሌላውን የስብእና ድክመት በመጠቀም የራሱን ፍላጎት ብቻ ከማራመድ ሊታቀብ ይገባል:: በፍቅር ግንኙነት ውስጥ የሌላውን ድክመት መሸፈን እንጂ ያንን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ የትዳር ጓደኛው ወደ ክፋት መምራት የወዳጅ ሳይሆን የጠላት ሥራ ይሆናል::

የአክዓብንና የኤልዛቤልን የትዳር ግንኙነት ስትመለከቱ ለግል ሕይወታችሁ ምን ትማራላችሁ? ከእነርሱ ጋር የምትመሳሰሉበት ነገር ይኖራል? የትዳር ግንኙነታቸው እግዚአብሔርን እንዲያስከብር፣ ሁለታችሁንም የሚያስደስት እንዲሆንና ሌሎች ሰዎችንም እንዲያንጽ ምን ገንቢ እርምጃ መውሰድ ይገባችኋል?